# ዕንባ ያስነባቹህ



ጉልበት የበላችሁ ፣ ደሃ ያሳዘናቹሁ፣
በሰው ላብ ኖራችሁ ፣ ልጅ ያሳደጋቹሁ፣
ሰውን በድላችሁ ፣ ዕንባ ያስነባቹሁ፣
የናንተ ቤት ሲሞቅ፣ ደሃውን ጥላችሁ፣
ባጣ እየኮራችህ ፣ እናንተ የሳቃቹሁ።
ጌዜ መስታወት ነው ይህንን አሳየን፣
በጎዳና ወድቆ የተበተነውን፣
ላገሩ የሰራውን ፣ ላስቲክ አልብሳቹሁ፣
ጀግና አሳንሳችሁ ፣ መንገድ ላይ ጥላችሁ፣
ዋጋ አሳጥታችሁ ፣ ጠሩን አፍርሳችሁ፣
በጎዳና ወድቆ ፣ ተመጭዋች አርጋችሁ፣
የእናንተ ቤት ሲሞቅ፣ ደሃውን ጥላችሁ፣
ክፋት ቆልላችሁ፣ እንደ ሕንጻ ቁመት፣
ሃገር የማትወዱ ፣ የኢትዮጵያ ጠላት፣
ይህ ብልጠት መልሷችሁ፣ የተደሰታችሁ፣
ሕዝቡን ቦጥብጣችሁ፣ ደሙን ጠጥታቹሁ፣
ቁም ስቃይ አብልታቹሁ፣ እያሰቃያችሁ፣
በቁመና ሞትን ፣ የሞት ሞት ሞታችሁ፣
የምድር እርግማኖች ፣ ሰው የተጠየፋችሁ፣
መልሱ የሰው ገንዘብ ፣ ምንም አይጠቅማችሁ።
ፀሃይ አዘቅዝቆ ፣ ጀምበሩ ጠለቀ፣
በላስቲክ ቤት ያለ ፣ ሱሪ የታጠቀ፣
ነገ የሱ ቀን ነው ፣ ጎሁ የሚቀደው፣
ደሃው ይታደጋል ፣ ጠላት ሱሪ ያወልቃል፣
እመነኝ ልንገርህ ፣ ይህን አስተውለው፣
እንደ ድመት ሆነህ ፣ ከስሩ የምትወድቀው፣
ሰዓቱ ነጎደ ፣ መመለሻም የለው፣
የምድር እርግማኖች ፣ ሰው የተጠየፋችሁ፣
መልሱ የሰው ገንዘብ ፣ ምንም አይጠቅማቹሁ፣

ብትወዱም ባትወዱም ፤ ስልጣን መልቀቃችሁ፤
ቅርብ ነው ሰዓቱ ፤ መሰናበቻችሁ።






መይሳው ከምድረ ስዊድን
2017-08-05